# ኢትዮሚዲያ
## ርእሰ አንቀፅ

# ሌቦች! የማንን እከክ በማን ማላከክ!
### ትርጉም ጠጅቱ ዲባባ

ትርኢቱ በኢትዮጵያ ሁሉ እየተለመደ መጥቷል:: ማጭበርበር ሲኖር ፣ በስልጣን መባለግ ሲከሰት፣ ብኩንነት ሲኖር፣ አስተዳደር ሲጎድል፣ የችሎታ ማነስ ሲከሰት፣ ወይንም በይፋ ለህዝብ ሲገለጽ የገዢዉ ወገን ጥቂት ማሳበቢያ (ማላከኪያ) ሰዎችን ወደ እስር ቤት ላከ:: አሁን በቅርቡ ወርቅ ከባንክ ቤት መወሰድ ታሪክ እየተነገረና እየተወሳ ነዉ ያለዉ:: በርካታ ሰዎች ትክክለኛዉን ወርቅ ሆነ ብለዉ ከባንክ ካዝና በማውጣትና በመውሰድ ወይም በምትኩ የሀሰተኛዉን ወርቅ በመተካት አልጠግብ ባይ ነጋዴዎች ሰበብ በእስር ቤት ታጭቀዉ ይገኛሉ:: አሁን በባላገሩና በከተማዉ የሚታየው የኢኮኖሚ ውድቀት የሚመሳሰለው የምፃት ዘመን ስጋና ነብስ ሲለያዩ ነብስን ይዞው ከሚሄዱት የአፐክሊብስ አራት ፈረሰኞች የአንዳኛው ተግባር ተምሳሌት ማለት ነው። በርካታ የስለላ ሰዎች ፡ ዘብ ተባቂዎች ፡ ተቆታጣሪዎች ፡ ነጋዴዎች እና ገንዘብ መንዛሪዎች ለዚህ ሁሉ ጥፋት ተወንጅለው የምግብ ዋጋን በማናር እስር ቤት ወርደዋል። በኢትዮጵያ እጅግ በጣም የናረ የኑሮ ዉድነትን ያመጣዉ "የአለም ገበያ" ሁኔታ ነዉ በማለትም አገዛዙ ያሳብባል:: እንዲሁም ዝናብ እንዳይጥል እግዚአብሔር በመያዙ ዘጠኝ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ለረሀብ በመጋለጣቸው እንደዚሁም እንደስይጣን በሚቆጥራቸው ተቃዋሚዎችም ያሳብባል::

አገዛዙ ስለ ኢትዮጵያ ፓለቲካና ኢኮኖሚ ችግር ሁሉንም መዉቀስ ይወዳል:: ለራሱ ግን ጥሩ እንደሰራ ምስጋና እንዲሰጠዉ ይሻል:: የሚጨነቀዉም ለምስጋና ብቻ ነዉ:: በሙሉ ድፍረት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማደጉ አስታዉቋል:: 10 ከመቶ ላለፉት አምስት አመታት ማደጉን፣ በ2000 ዓ.ም ደግሞ የዕድገት አመት 10.8 ከመቶ ወደ ዉጭ ንግድ በ32 ከመቶ ባለፉት ስምንት ወራት ዉስጥ መጨመሩን፣ የእህል ምርት በ 45 ከመቶ ባለፉት አምስት አመታት ዉስጥ ከፍ ማለቱን፣ አዲስ አበባ ህንፃዎች በየቀኑ መሰራት የአፍሪካ ዋና መዲና ሆና ማደጓን ያመለክታል። ከአንድ ችግር በስተቀር ሁሉን ነገር ካብ ካብ ነዉ:: ይኸዉ አገዛዝ ሃላፊነት ያለበትን ቦታ በሙሉ በመዉረር ልክ ጣፋጭ ፍሬን እንደመሰብሰብ የራሱን የስራ ዉጤት ሲያደንቅ ይታያል:: ጫማ ላንድ ሰዉ ልክ ከሆነ ያሰዉ ይለብሰዋል እንጂ ለሌላ ሰዉ አያስተላልፈዉም:: አብሮ አታሎ ሌላው ብቻ እንዲወቀስ የሚደረገዉን ታሪክ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ልንገዛ አንፈልግም::

**ማላከክ ቁጥር #1፡ ዘራፊ ልቦች ወይም የባንክ ደደቦችና ቁጥራቸው**

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ሲነገረን የቆየዉ ታሪክ ቢኖር የኢትዮጵያ ባንክ በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት ወርቅ ክምችት ተጠርጎ መወሰዱን ነዉ::የተደራጁ

ዘራፊዎች፣ ሰራቂ ልቦች፣ሽብርና ችግር ፈጣሪዎች ወደ ባንክ በመሄድ በብዙ መቶ የሚቆጠር የእዉነት ወርቅ በወርቅ ቅብ በመለወጥ ያወጡ ይሆናሉ ወይም ደግሞ ደደብ ባንክ ባለስልጣናት  በሚሊዮን ብር የሚያወጣ ወርቅ  ሲገዙ የገዙት ትክክለኛ መሆኑን ሳያረጋግጡ ግዥ ፈጽመው ይሆናል::  እንዲህ አይነቱ የሌቦች ቡድን ወይም የደደብ ባንክ ባለስልጣናት ዘረፋ ማካሄድ ተረት ተረት ታሪክን ከማመን የፋሲካ ጥንቸልንና የገና የሳንታ ክሎዝን ማመን ይሻላል::

## ማላከክ ቁጥር 2፡ ሰላዮች፡ ዘብጠባቂዎች፡ተቆጣጣሪዎች አትራፊዎችና የዉጭ ገንዘብ መንዛሪዎች።

ሰላዮች፡ ዘብጠባቂዎች፡ተቆጣጣሪዎች ፡አትራፊዎችና የዉጭ ገንዘብ መንዛሪዎች፡በቅርቡ ለአገሪቷ ኢኮኖሚ ዉድቀትና የኑሮ ዝቅተኝነት አዲስ ተወቃሽ ቡድኖች ሆነዉ ቀርበዋል::  እነዚህም አትራፊዎችና መንዛሪዎች በተለይ ገበሬዎች ናቸው የምግብና የአንዳንድ አስፈላጊ ነገሮችን አቅርቦት ማሳነስና ዋጋ መጨመር ለገበያው ዋጋ መናር ምክንያት ሲሆኑ ሕገወጥ የዉጭ ገንዘብ መንዛሪዎችም  የጥቁር ገበያ ሸማቾች የአለዋወጡን ሁኔታ ዉጣ ዉረድ ፈጠሩ በኢኮኖሚዉ ላይ ከፍተኛ ቀውስ  ጣሉ::  ይህ ሁሉ ግን የእናቴ ቀሚስ አድናቀፈኝ አይነት ሰበብ ነው የሚቀርበው። ይህንኑ አስመልክቶ የተባበሩት መንግስታት  ሲናገር የእርሻ ዉጤቶችን አቅራቢዎችና ነጋድዎች ለዕቃዉ እጥረትና ለዋጋዉ መጨመር ተወቃሾችና ሃላፊዎች ሊሆኑ አይገባም::  እነዚህም ወንጀለኞች ናቸዉ ከተባለ መንግስት ይህን ለይቶ ማዉጣቱና ችግሩን በጊዜ ለማስተካከል ለምን ብዙ ግዜ ወሰደባቸው::

## ማላከክ ቁጥር 3 የዓለም ንግድ

በትንሹ ለምግብ እጥረት ለገበያ ውጣ ውረድና ለመሳሰሉት ብሄራዊ ለኢኮኖሚው በቁጥጥር ስር ነው።ይህም በአምስት ዓመት ውስጥ የታየ እውነታ ነው። የዉጭ ንግድ በ32 ከመቶ ባለፉት ስምንት ወራት ብቻ አድጓል::  ሆኖም የኢትዮጵያ ኑሮ ሁኔታ ከሚገባዉ በላይ ውድ ሆኗል ::  ይኸው "የዓለም ንግድ" በኢትዮጵያ ላይ ጫና በመፍጥሩ ነው። አበቃ! ::  ሆኖም "ጉዳዩን በቁጥጥር ስር ልናደርገው የኢኮኖሚ ችሎታ ብቃት የለንም" "በመጥፎው የዓለም ዓቀፍ ንግድ ጫና የተጎዳን ነን ፡ምን ማድረግ እንዳለብንም አናዉቅም::"

## ማላከክ ቁጥር 4 እግዚአብሔር/ፈጣሪ

ድርቅ በጥቁር ፈረስ ተጭኖ የምፃት ቀኑን እያቀረበብን ነው።በአብዛኛው በምስራቅና በደቡብ ኢትየጵያ ከፍተኛ ረሃብ (የምግብ እጦት ) ተከስቷል:: ለብዙ አመታት ረሃብ በዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ መግለጫ ሆኗል::የሰብአዊ መብት ተመልካችና ለሰዎች ደህንነት የሚታገሉ ድርጅቶች በሰጡት አስተያት "በ2000 ዓ.ም

ሰምንት ሚሊዮን ሕዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን አንድ ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ በአስቸኳይ ዕርዳታ ስር የወደቁ ናቸው" ሲሉ የጉዳዩን አሳሳቢነት ዘግበዋል:: በግልጽ እንደሚታወቀው ሁሉ ለአገሪቷ የምግብ መናርንና ለረጅም ጊዜ እቅድ መያዝን በተመለከተ አንድ አካል ሃላፊነትን መዉሰድ አለበት :: ነገር ግን ይህ ሁሉ ነገር በአምላክ እጅ ነው:: ለማናቸውም ጉዳይ ስለረሃብ ሲነሳ የሚወሰደው "ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ስላልጣለ በፍጥነት በማደግ ላይ ያለውን የኢኮኖሚያችን እድገት ሊጎዳ አይችልም።" እግዚህአብሄር ላለፈው ዓመት ዝናብ ስላልላከልን ረስቶናል:: በመሆኑም በመጨረሻ ስሌት ሊከሰት ለሚችለው ምግብ እጥረትና ረሃብ ሓላፊነቱ የእግዜብሄር ነው:: ( ለማንኛውም እነዚያ ሰዎች ለምን ኬክ አይበሉም? )

## ማላከክ ቁጥር 5 ታቃዋሚ ፓርቲ

ለማንኛውም ነገር ተወቃሹ ወያኔ /ኢሐዴግን ተቃዋሚ ነው:: ቅኝጅት የ1997 ዓ. ም ምርጫ ባያሸንፍ ኖሮ ሁሉ ነገር በመልካም ይካሄድ ነበር ::በመደዳ የሰዉ ልጅ መብት መገፈፍ አይኖርም ነበር:: በሙቶና በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች እስር ቤት አይወረወሩም ነበር:: አንድ ሙቶ ዘጠና አንድ ሰዎች ለሞት አደጋ በልተጋለጡ ነበር:፤ በሺህ የሚቆጠሩም አይቆስሉም ነበር፤የሲቭል ማህበራት አያስፈልጉም ነበር፤ የሕግ የበላይነትና ሌሎች የዲሞክራሲ መሰረታዊ ጉዳዮችም ባልነበሩ፤፡(ሶማሊያ የሚባል ነገር ባይኖር ጥሩ ነበር) ። በአሜሪካ ምክር ቤት የሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ ኤች አር 4421፤ኤች አር 5680 ወይም ኤች አር 2003 ባላስፈለገም ነበር:: በምንም መልኩ የተተያቂነት የሚባል ጥያቄ ባልትነሳ ነበር።በእርግጥ ተቃዋሚ ባይኖር ኑሮ ኢትዮጵያ የተለየ የፖለቲካ ፈንጠዝያ የሰፈነባት ትሆን ነበር::

## አጠቃላይ የአመራር ውድቀት

ለፖለቲካ መሪ ከባድ ወቅት የሚባለው ለፈጸመው ስህተትና ድክመት ሃላፊነት መውሰድ መቻልና አለመቻል ላይ ነው :: ጆም ኮሊን የተባለው ታላቅ መምህር እንደሚለው ለብዙ የዓለም ከፍተኛ የስራ አስፈጻሚዎች ለድርጅቶች፤ለመስሪያ ቤቶች ለማሕበራትና ለተቋማት እድገት መልካም መሪ በተከታታይ ለሌሎች ስራ ዋጋ ሲሰጥና ውስጣዊ ጉዳዮችን ይመረምራሉ ፤ለድርጅቶች፤ለመስሪያ ቤቶች ፤ለማሕበራትና ለተቋማት እድገት መልካም እድል ሲለፋ ነው የሚታየዉ::ስህተትም ሲከሰት በሙሉ ሀለፊነቱን ይወስዳል።ለመሸፋፈን ወዲያ ወዲህ አይራወጥም፤ በሰዎችም አያላክክም። መቼ ይሆን የኢትየጵያ መሪ ለፈጸማቸዉ ስህተቶችና በአገሪቷ ላይና በሕዝቡ ላይ ላደረስዉ የሕይወት መጥፋት፤ የኢኮኖሚ ውድቀትና ለሃብቷ መሰረቅና መበዝበዝ ሓላፊነትን የሚወስደው?

**በመጨረሻም ኢትዮጵያ  የሌቦች መዲና ሆነች?**

ምንም ሊካድ  የማይቻል ነገር ቢኖር ሌቦች  በኢትዮጵያ በየቦታዉ ነዉ ያሉት:: ፖሊሶች  የሚደርሱት ሌባው በይፋ ሰውን በአደባባይ ነጥቆ ከሮጠና ባንኮች ከተዘረፉ በኃላ ነው:: ወንጀሉ ከተፈጸመ ካንድ ቀን በኃላም የሚደርሱበት ሁኔታም ብዙ ነው። (የገንዘብ  እጥረት  ግን ፈጽሞ አያውቃቸውም)  እንዲሁም ብለው ሌቦቹ ላይ ምስክር ለሆኑ የሚችሉትን እስር ቤት ይከታሉ ፤በሌቦቹ ላይ እንዳይመሰክሩ ያደርጋሉ::  በዚህ ሁኔታ ፖሊሶቹን በቡድን ከሚዘርፉ ሌቦች ለይተን ለማየት ያዳግተናል:።